# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 2 ቁጥር 79 መጋቢት 2 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## «ኢዜማ ቢመረጥ አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ከተማ እንድትሆን ይሠራል»ክቡር ገና



# «ኢዜማ ቢመረጥ አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ከተማ እንድትሆን ይሠራል» ክቡር ገና

የዛሬው የዜጎች መድረክ የ ‹‹ቆይታ›› አምድ እንግዳችን ኢዜማን በቅርቡ የተቀላቀሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ክቡር ገና ናቸው፡፡ ክቡር ገና በ6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ ኢዜማን በመወከል ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት እንዲወዳደሩ በምርጫ ወረዳ 21/22 ተመርጠዋል፡፡ ከእሳቸው ጋር ያደረግነውን ተከታዩን ቆይታ እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡



*የፓርቲ ፖለቲካ ውስጥ ለመሳተፍ ሲወስኑ ኢዜማን ለምን ምርጫዎት አደረጉ? ለምንስ እስካሁን የፖለቲካ ተሳትፎ አላደረጉም?*

ኢዜማን ምርጫዬ ያደረኩበት ምክንያት የዘር ፖለቲካን የማይቀበል፣ የኢትዮጵያ አንድነት የሚያስጨንቀው፣ ማኅበራዊ ፍትህን የሚከተል እንዲሁም የድህነት ቅነሳ ላይ የሚሠራ ፓርቲ በመሆኑ ነው፡፡

የፖለቲካ ተሳትፎዬን በተመጠ ለከተ ከዚህ በፊት ፖለቲካዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ስሰጥ ቆይቻለሁ፡፡ በተለያዩ መድረኮችም ቀርቤ ከፖለቲከኞች ጋር ተወያይቻለሁ፡፡ በእርግጥ ፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ገብቼ ተሳትፎ አድርጌ አላውቅም፡፤ ለሁሉም ጊዜ አለው ይባል የለ?

*ለክቡር፣ አዲስ አበቤነት ማለት ምን ማለት ነው?*

በቀላል አገላለጽ አዲስ አበቤ **ነኝ ስል የአዲስ አበባ ተቆርቋሪ ነኝ ማለት ነው፡፡ በአሜሪካን አገር በ**ኒውዮርክ ከተማ ትምህርቴን ስከታተልም ሆነ ሥራ ስሠራ አዲስ አበባ ከልቤ አልጠፋችም፡፡ ለእኔ አዲስ አበቤ ማለት ከቤቱ ሲወጣ የሰፈሩን ነዋሪ እንዴት አደራችሁ ብሎ፤ ግራ ቀኙን አካሎ፤ ያለ የሌለውን የከተማዋን ውበት ቃኝቶ በቅልጥፍና የዕለቱን መሰናክሎች አልፎ በሰዓቱ የሚከሰት ማለት ነው፡፡ አዲስ አበቤ ቻይ ነው፤ ሲፈልግ ቆጣ ሳይፈልግ ደግሞ ልቡን ከፍቶ በፈገግታ ኑሮውን የሚገፋ ነው፡፡

*የአዲስ አበባ አንዱ መሰረታዊ ችግር የስነ- ሕዝብ (ቁጥር) መናር ነው፤ለዚህ መሰረታዊው መፍትሄ ከተማዋን እድገት ወደ ሌሎች ከተሞች ማሰራጨት እና በከተማዋ ውስጥ ያሉ ፌደራል ተቋማትን በከፊል ወደ እነርሱ መውሰድ ነው የሚሉ አስተያየቶች አሉ። (ከገጠር ወደ ከተማ ያለው ፍሰት አንዱ ገፊ ምክንያት ነውና) በዚህ ላይ ምን አስተያየት አሎት?*

የሕዝብ ቁጥር መናርም ሆነ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰው ሕዝብ ቁጥር መጨመር የከተማዋን የፖለቲካም ሆነ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን አቅም መፈታተኑ አ**ይ**ቀርም። **በሂደትም** የ**ከ**ተማዋን ህልውና ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል። የአዲስ አበባ ከተማ የወደፊት እድገትን በእቅድና በዘዴ መተለም ያስፈልጋል።

ይህንንም ችግር ለመቅረፍ አዲስ አበባ ከተማ ባቅራቢያዋ ከሚገኙ የኦሮምያ ከተሞች ጋር በሕብረት መሥራት ይኖርባታል፡፡ የመኖሪያ **ቤ**ቶች የንግድና የአጠ ,ንድስትሪሥ የመሠረተ ልማት ግንባታን አብሮ ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡ ለወጣቶች የሥራ እድል እንዲጨምር ማድረግም ግድ ይላል፡፡ በዚህ ሂደት ሌሎች የክልል ከተሞችም እያደጉና እየበለፀጉ ስለሚሄዱ ወደ አዲስ አበባ የሚፈልሰውን ሕዝብ መቆጣጠር ይቻላል፡፡

*ኦሮሚያ በአዲስ አበባ ላይ ልዩ ጥቅም እንዳታገኝ ሕገ መንግስታዊ መሰረት ተሰጥቷታል፤ በዚህ ላይ ምን አስተያየት አሎት?*

አዲስ አበባ የኢትዮ**ጵያ ዋና ከተማ ናት፤ አራት ነጥብ**፡፡ ልዩ ጥቅም፡፡ የሚባለውን ነገር በትክክል ይህ ነው ብሎ ለመናገር አይቻልም፡፡ ልዩ ጥቅም ሲባል **ፍቺው** በግልፅ መታወቅ መቻል አለበት፡፡

*አዲስ አበባ ራሷን የቻለች ክልል ትሁን የሚሉ ድምጾች አሉ፤ አዲስ አበባ ክልል በመሆን/ አለመሆን ምን ታጣለች/ ትጠቀማለች?*

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለማን ይሁን የሚለው በቅድሚያ መመለስ አለበት፡፡ አዲስ አበባ ተጠሪነቷ ለነዋሪዎቿ መሆን አለበት የሚለው አስተሳሰብ እንዳለ ሆኖ፤ የአገሪቱ ዋና ከተማ እና የፌዴራል መንግሥት መቀመጫ እንደመሆኗ የፌዴራል መንግሥትና የከተማዋ አስተዳደር አብረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

*ኢዜማ ለአዲስ አበባ ምን ዓይነት የከተማ ልማት ፖሊሲ ያስፈልጋታል ብሎ ያምናል?*

ፖሊሲዎቻችን የከተማችንን ችግሮች የሚፈቱ ሆነው የተቀረፁ ናቸው፡፡ ከዚህ በፊት ጥሩ ውጤት ያመጡ ሥራዎችን የበለጠ በማስፋፋት እንዲሁም አዳዲስ የነዋሪውን ቀዳሚ ችግሮችን ለመፍታት የሚችሉ ፖሊሲዎችን በመንደፍ ውጤት ተኮር ለውጦችን ማስተናገድ ያስፈልጋል፡፡ አብሮና ተደጋግፎ መሥራትን ቅድሚያ የሚሰጡ ራስን መቻልና የኑሮ ውድነትን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ላይ ርብርብ ይደረጋል፡፡ ትምህርት እና ጤና ላይ እንዲሁም የመኖሪያ ቤት እና የትራንስፖርት ችግሮችን የሚቀርፉ ፖሊሲዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ቅድሚያ እንሰጣለን፡፡

*በአዲስ አበባ ሕገ ወጥ መልክ የተወረሩ መሬቶችና በኢ-ፍትሐዊ መልክ የታደሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይገባል?*

የተወረሩ መሬቶችም ሆኑ ያላግባብ የታደሉ የጋራ መኖሪያ ቤ ቶች በሕጉ መሠረት ሥርዓት እንዲይዙ ሥራ ይሠራል፡፡ **ይህ ሲባል ግን** ሰዎች ጠራራ ፀሐይ ላይ እንዲወድቁ ይደረጋል ማለት አይደለም፡፡ በተቻለ መንገድ የችግሩን ጥልቀት በመገምገም መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ አሠራሮችንም በመለየት ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ይህ ችግር እንዲወገድና ተመልሶም እንዳይከሰት፣ ተጠብበን እና ተጨንቀን መሥራት ይኖርብናል፡፡ ነዋሪዎችም የተስተካከለና በጥሩ ሁኔታ ህይወታቸውን የሚመሩበት ከተማ እንዲኖረን በጋራ መሥራት አለብን፡፡

*ከሕዝብ ቁጥራችን አብዛኛውን ቁጥር የሚይዘው ወጣቱ ክፍል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በከተማ ውስጥ ያለውን የወጣት ሥራ አጥነት ለመፍታት ምን መደረግ አለበት ይላሉ?*

ዛሬ ወጣቱ ቢያንስ አራትና አምስት ነገሮችን ይጠብቃል፡፡

1ኛ ሥራ ይፈልጋል፡፡ ዛሬ በቀላሉ ሥራ ለማግኘት አይችልም፡፡ ስለዚህ ራሱን ችሎ ህይወቱን ለማሳካት የሚጠ ችልበትን ሥልጠና፣ ካፒታልና ለምርቱ ገበያ የሚያገ**ኝበትን** *መንገድ ማመቻቸት* አለብን፡፡

2ኛ ለዘመኑ የሚጠቅም ዕውቀት የሚያገ**ኝበትን** ትምህርት ቤቶች *ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ወጣቶቻችን ማንበብና መፃፍ ይቸገራሉ፡፡ የእንግሊዘኛ ቋንቋም ሆነ ጽሑፍ አይችሉም፡፡ እነዚህን ለማስተካከል የተለያዩ ማሻሻያዎች ማድረግ ያስፈልጋል፡፡*

3ኛ ወጣቱ ከሱስና ከአልባሌ ድርጊቶች እንዲቆጠብ በስፖርት፣ በሥነ ጥ በብ እና የበጎ አድራጎት ሥራዎች እንዲሳተፉ በማድረግ የራሱን ዕድል በራሱ የሚወስንበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

4ኛ ከሙስና የፀዳ አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ወጣቶቻችን ሙስና በህይወታቸው ላይ እያመጣ ያለውን ጉዳት ይገነዘባሉ፡፡ የወደፊት የወጣቱ ተስፋ እንዳይቀጭጭ ሙስናን ከከተማችን ብሎም ከአገራችን ለማጥፋት በትኩረት መሠራት አለበት፡፡

5ኛ ወጣቱ የህይወት ክህሎቱን የሚያነብበት ምክር ሰጪ ያስፈልገዋል፡፡ ስለሚጠብቀው ዓለም እንዲሁም ህይወቱን የሚያሻሽልበት መንገዶች የሚያመላክተው ያስፈልገዋል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

መጋቢት 2 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

*ከገጠር ወደ ከተማ በከፍተኛ ቁጥር እየፈለሰ የሚገኘውን ወጣት ፍልሰት በምን መልክ መቆጣጠር ይቻላል?*

ከገጠር ወደ ከተማ የሚከሰተ ውን ፍልሰት ለማቆም ቀላል አይደለም:: በመጀመሪያ ፍልሰቱ ለምን መጣ ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል:: የችግሩ መፍትሄ ይህን ጥያቄ በትክክል ስንመልስና የወጣቱን ፍላጎት ለማሟላት ተግተን ስንሠራ እናገኘዋለን:: የጤናሥ የትምህርትሥ የሥራሥ የመዝናኛ... በተለይም የእድገት ዕድሎች ገጠር እንደልብ ስለማይገኙ እንዲሁም የእርሻ መሬት ሲጠብ ወይም ሲጠፋ ፍልሰት ይጨምራል::

*የአዲስ አበባን ሕዝብ በከንቲባነት የማገልገል ዕድሉን ቢያገኙ ለሕዝቡ ምን ይሰራሉ?*

እኔ ብቻዬን ብመረጥ ምንም ፋይዳ የለውም:: ነገር ግን ኢዜማ ቢመረጥ አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ከተማ እንድትሆን ይሠራል:: የነዋሪውን ዋና ዋና ችግሮች ለመፍታት በተለይም የኑሮ ውድነትሥ የመኖሪያሥ የትራንስፖርት ችግሮችን ለመፍታት ትኩረት እንሰጣለን::

ዋናው ሥራችን ግን የአዲስ አበባ ወጣት ሥራ እንዲያገኝና ራሱን ችሎ ቤተሰቡን እንዲያስተዳድር መደገፍ ይሆናል:: ሌሎች ልንሠራቸው ያቀድናቸው የሥራ ዝርዝሮች በቅርቡ ይፋ ይደረጋሉ::

*ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅትን (WTO) ከሁለት ዓመት በኋላ ትቀላቀላለች ተብሎ እየተጠበቀ ነው፤ በእርግጥ ይጠቅመናል?*

ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታትየዓለም የንግድ ድርጅት (WTO) አባል ትሆናለች ሲባል ዘመናት አስፋ እኮ:: ለማንኛውም የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) የሚባለው ድርጅት ጊዜው ያለፈበት ዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅት ነው:: በግሌ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አባል መሆን ምንም ለውጥ አያመጣም ባይ ነኝ::

*የኢትዮጵያ ብር ከሌሎቹ በተለይ ከዶላር አኳያ እጅጉን እየወደቀ (ዲፕርሼት እያደረገ) መሆኑ ይታወቃል፤ መንግሥትም የውጭ ምንዛሪውን በገበያ ሕግ እንዲመራ ፍላጎት እንዳለው ተናግሯል፤ ይሄ ደግሞ የአገሪቷን የውጭ ንግድ ሚዛን (ባላንስ ኦፍ ፔይመንት) የበለጠ እያዛባው አይሄድም?*

እንደሚታወቀው የአገራችን የገቢ ንግድ ከወጪ ንግዷ በከፍተኛ ሁኔታ በልጦ ለዘመናት ቆይቷል:: ይህን በአንድ ጊዜ ለመለወጥ ያስቸግራል:: በሀገር ደረጃ ኤክስፖርትን ለማሳደግ ብዙ ይጣራል:: ችግሮቹ በርካታና ውስብስብ ናቸው:: ሆኖም ኤክስፖርት በውድድር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የዓለም አቀፉ ገበያ የሚጠይቀውን ምርት ለማቅረብ አቅማችንና ጉልበታችንን ማጎልበት ያስፈልጋል:: አሁን እያመረትን ያለው ምርትና አገልግሎት በዓለም ገበያ ተፈላጊነቱን ገምግመን መንቀሳቀስ ያስፈልጋል:: በቅርቡ የአፍሪካ ነፃ ገበያ ስምምነት መፈረማችን ይታወሳል:: ይኸንን የነፃ ገበያ እድል መጠቀም ሌላኛው ኤክስፖርትን ማስፋፊያ ዘዴ ነው:: ሌሎች ሁለት ሀሳቦችን ልጨምር:: ይኸውም በአሁኑ የንግድ ዓለም አጋር ይዞ መጓዝ ለተሻለ ኤክስፖርት ውጤት በር መክፈት ሲሆን በተለያዩ የንግድ ትርኢት መካፈልም እንደዚሁ ሌላኛው የኤክስፖርት በር ከፋች ነው::

የብራችን መውደቅም በየኪሳችን የምናየው ነው፤ ዛሬ ዛሬ በየቀኑ እየደኸየን እንጂ እያደግን አይደለም:: ብር እየሞሸሸ ኤክስፖርት አደገ፤ አገር ትበለፅጋለች ብሎ መለፈፍ የሞኝ አስተሳሰብ ነው::

*ወሳኝ የሚባሉ ሕዝባዊ የንግድ ተቋማትን ፕራይቬታይዝ ማድረግ ለኢትዮጵያ ይጠቅማል ብለው የሚከራከሩ ልሂቃን አሉ:: እርሶ ደግሞ በዚህ እንደማይስማሙ በአንድ ፅሁፎት ላይ ገልፀዋል:: እንደ ኢትዮ ቴሌኮም ያሉ የአገር አንጡራ ሀብት ፕራይቬታይዝ ማድረግ የሚያስከትለው አሉታዊ ነገር ምንድን ነው?*

መልሱ ቀላል ነው:: በሕዝብ ቁጥጥር ኖሮ እያተረፈ ያለ ድርጅት ለፈረንጅ የሚሸጥበት ምክንያት ምንድን ነው? ያውም ባለቤቱ ለማይታወቅ ግዙፍ ድርጅት:: ራሱን እንዲህ ዝቅ አድርጎ ስለ ወደፊት እድገት የማያስብ መንግሥት ማየት ያሳዝናል:: እዚህ ጉዳይ ላይ ተጠቃሚው ማነው? የቴሌ ገዥው ወይስ እኛ የተፈረደብን ሸማቾች?

*ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ሕወሓትን መደምሰሳቸውንና ኢሕአዴግን አፍርሰው በራሳቸው አምሳል ብልፅግና የሚባል ፓርቲ መመስረታቸውን ተከትሎ ከምርጫ በኋላ "benevolent dictator" ይሆናሉ የሚሉ አካላት አሉ:: በዚህ ይስማማሉ?*

በቋንቋችን ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ጥሩ ወይም መጥፎ አምባገነን ይሆናሉ ብሎ ከወዲሁ መተንበይ አይቻልም:: ሕዝብ የሚወደውና የሚፈቅደው አምባገነን ሲኒማ ውስጥ ካልሆነ በገሀድ ዓለም ብዙ አይታይም::

*ኢዜማ ልሂቅ የሚባለውን የማኅበረሰብ ክፍል ብቻ ቀልብ የያዘ ፓርቲ እንደ መሆኑ መጠን ምርጫ የማሸነፍ እድሉ ጠባብ ነው የሚሉ አሉ:: ይህን አስተያየት ይቀበሉታል?*

ኢዜማን በሚመለከት እኔ የተለየ እይታ ነው ያለኝ:: የልሂቅ ፓርቲ ሩቅ አይሄድም:: ኢዜማ የወጣቶችና በወጣቶች የሚመራ ፓርቲ መሆኑን ነው ያስተዋልኩት:: የአሸናፊነት ስሜት አያለሁ:: የተስፋ ስሜት የሰፈነበት ቤት ነው:: ረጋ ብሎ ግራና ቀኙን አመዛዝኖ የሚጓዝ ሰላማዊ ፓርቲ ነው:: በዚህ ምርጫ ለመወዳደር መዘጋጀቱ ራሱ አሸናፊ አድርጎታል::

*ስቃስምልልሱ ፍቃደኛ ሆነው ከእኛ ጋር ቆይታ ስላደረጉ በአንባቢዎቻችን ስም ምስጋናዬ ይድረስዎት::*

እንግዳ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ፤ እኔም አመሰግናለሁ::





# ኢዜማ፣ በባህር ዳር እና በደብረ ብርሃን ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባ አዘጋጀ

መጋቢት 02 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የፊታችን እሁድ መጋቢት 5 ቀን 2013 ዓ.ም በባህር ዳር እና በደብረ ብርሀን ከተሞች ከከተማው ነዋሪዎች፣ ደጋፊዎች እና ኢዜማ አባላት ጋር የሚወያይ ይሆናል::

ኢዜማ በተመረጡ 42 ከተሞች ላይ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ለማካሄድ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ እንዳለ የሚታወቅ ነው:: ፓርቲው የምርጫ ዘመቻ ማስጀመሪያውን የካቲት 13 ቀን 2013 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በግዮን ሆቴል ካስጀመረ በኋላም በጋምቤላ፣ በወልዲያ፣ ደሴ እና አርባ ምንጭ ከተሞች ላይ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ማካሄዱ የሚታወስ ነው:: በያዝነው ሳምንትም በባሕር ዳር እና ደብረ ብርሀን ከተሞች ከከተማው ነዋሪዎች፣ ደጋፊዎች እና የኢዜማ አባላት ጋር የሚወያይ ይሆናል::

የኢዜማ ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት እሁድ መጋቢት 5 ቀን 2013 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ጀምሮ በደብረ ብርሃን ከተማ በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ህንጻ የመሰብሰብያ አዳራሽ ከሕዝብ ጋር ውይይት የሚካሄድ ሲሆን በተመሳሳይ ሰአት በባህር ዳር ከተማ በሙሉዓለም የባሕል ማዕከል አዳራሽ ሕዝባዊ ውይይት የሚካሄድ ይሆናል:: በደብረ ብርሃን ከተማ የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ (ዶ/ር) እና ሙሉዓለም ተገኘወርቅ (ዶ/ር) የሚገኙ ሲሆን፤ በባህር ዳር ከተማ የኢዜማ ምክትል መሪ አንዷለም አራጌ፣ ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ እና ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ናትናኤል ፈለቀ ከሕዝብ ጋር ለመምከር የሚገኙ ይሆናል::

ኢዜማ፣ የካቲት 08 ቀን 2013 ዓ.ም የምርጫ ቅስቀሳ በይፋ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በጋምቤላ፣ በአርባ ምንጭ፣ ደሴ እና ወልዲያ ከተሞች ሕዝባዊ ውይይት ማካሄዱ የሚታወስ ነው:: በሚመጡት ሳምንታትም በሌሎች ከተሞች ላይ ሕዝባዊ ውይይት በማካሄድ ከሕዝብ ጋር እየመከረ እንደሚቀጥል ያገኘነው መረጃ ያስረዳል::

# በዕጩ ምዝገባ ወቅት ስላጋጠሙ እንቅፋቶች ኢዜማ ማብራሪያውን ከመገናኛ ብዙሃን ያቀርባል

## የፓርቲው ማኒፌስቶም ይፋ ይሆናል

መጋቢት 02 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በዘጠኝ ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ዕጩዎቹን አስመዝግቦ ማጠናቀቁን የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገለጹ::

በዕጩዎች ምዝገባ ወቅት የገጠሟቸውን እንቅፋቶች ተከትሎ ለማስመዝገብ ያቀዷቸውን ያህል ዕጩዎች ማስመዝገብ እንዳልቻሉ የጠቀሱት ኃላፊው፣ በበርካታ እንቅፋቶች ውስጥ በማለፍ ምርጫ ከማይካሄድበት የትግራይ ክልል ውጪ በዘጠኙ ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ዕጩዎችን አስመዝግበው ማጠናቀቅ እንደቻሉ አስረድተዋል:: በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት ያጋጠሟቸው እንቅፋቶችን በሚመለከትም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር ሲነጋገሩ እንደቆዩ ጠቁመዋል:: ዕጩዎችን በማስመዝገብ ሂደት ስላጋጠሟቸው ፈተናዎች በዝርዝር ለመገናኛ ብዙሃን የፊታችን አርብ መጋቢት 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጋዜጣዊ መግለጫ እንደሚሰጡ ኃላፊው አስታውቀዋል::

ኢዜማ የፊታችን አርብ መጋቢት 03 ቀን 2013 ዓ.ም በዋና ጽህፈት ቤቱ በመስፍን ወልደማርያም አዳራሽ በሚሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ዕጩዎን በማስመዝገብ ሂደት ስላጋጠሙት ፈተናዎች እና ከፀጥታ ጋር በተገናኘ ባሉ ጉዳዮች ላይ መግለጫውን የሚሰጥ ሲሆን፤ በዕለቱ የፓርቲው ማኒፌስቶም ለመገናኛ ብዙሃንና ለሕዝብ ይፋ የሚደረግ ይሆናል::

# ኢዜማ በደሴ፣ ወልዲያ እና አርባ ምንጭ ከተሞች ከሕዝብ ጋር ተወያየ

መጋቢት 02 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ባሳለፍነው እሁድ የካቲት 28 ቀን 2013 ዓ.ም በደሴ፣ ወልዲያ እና አርባ ምንጭ ከተሞች ሕዝባዊ ውይይት አካሄደ፡፡ በደሴ ከተማ በተካሄደው ውይይት ላይ የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ (ዶ/ር)፣ የኢዜማ የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪ እና በጉለሌ ክፍለ ከተማ ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የኢዜማ ዕጩ የሆኑት አማን ይኹን ረዳ ተገኝተዋል፡፡ በደሴ በነበረው ሕዝባዊ ውይይት ላይ 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ ያለው አገራዊ ፋይዳ ምን እንደሚመስል በምክትል ሊቀመንበሩ ጫኔ ከበደ (ዶ/ር) አማካኝነት ለውይይት የሚሆን መነሻ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

ኢዜማ ምርጫው በሰላም ተጀምሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ ያለበትን አገራዊ ኃላፊነት በጥንቃቄ እንደሚወጣ የተገለጸ ሲሆን፤ ኢዜማ ኢትዮጵያ አሁን ከምትገኝበት ሁኔታ አንጻር የሕዝቡን ሰላም አስጠብቆ የልማት ጥያቄዎችን ለመመለስ ያለውን አማራጭ በሚመለከት የፖሊሲ አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡ 10ሩ የኢዜማ ግቦች እና ኢትዮጵያ የምትገኝበት መጠነ ሰፊ ችግሮች በሚመለከትም የፖሊሲ አስተባባሪው ማብራሪያቸውን አቅርበዋል፡፡ ከሕዝባዊ ውይይቱ ታዳሚዎች ለተነሱት ኢዜማ የትኞቹ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጾች እንዲሻሻል ይፈልጋል? ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫ ማካሄድ ይቻላል ብላቹህ ታምናላቹህ? ለደሴ እና ለአካባቢው ሕዝብ ምን አማራጭ አላቹህ? ለሚሉ ጥያቄዎችም ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በዕለቱም በደሴ ከተማ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤት የሚወዳደሩ ዕጩዎች ተዋውቀዋል፡፡

በወልዲያ ከተማ በተካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ የኢዜማ የፋይናንስ ኮሚቴ ኃላፊ አንድነት ሽፈራው እና በቦሌ ክፍለ ከተማ ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የኢዜማ ዕጩ የሆኑት ኢዮብ መሳፍንት የተገኙ ሲሆን መጪው 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ ያለው ታሪካዊ እና አገራዊ ፋይዳ ምን እንደሚመስል፣ ኢዜማ የምርጫ ዘመቻውን በምን መልኩ ለመምራት እንደተዘጋጀ እና የተዘጋጀበት ፍኖተ ካርታ ምን እንደሚመስል ለሕዝባዊ ስብሰባው ታዳሚዎች ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡ በተጨማሪም ኢዜማ ያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች እንዲሁም በሚመጣው አምስት ዓመታት ቢመረጥ ምን ለማድረግ እንደተዘጋጀ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

የምርጫ አስፈጻሚዎች ገለልተኝነት ምን ይመስላል? ምርጫው ላይ የተለያዩ ሰዎች የሚሳተፉበት እንደመሆኑ መጠን ከእነዛ ሰዎች ጋር ሊኖረው የሚገባው ግንኙነት ምን መምሰል አለበት? ብልፅግና እና ኢዜማ አንድ ናቸው ተብሎ ለሚነሳው አስተያየት እንዴት ነው ተገቢ ምላሽ መስጠት የሚቻለው? የዕጩዎች የምርጫ ሂደት ምን ይመስል ነበር? ከመሬት ባለቤትነት ጋር በተያያዘም ምን ዓይነት አማራጮች አላቹህ? ለሚሉ ከሕዝባዊ ስብሰባው ተሳታፊዎች ለተነሱት ጥያቄዎችም ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ኢዜማን በወልዲያ ወክለው የሚወዳደሩ ዕጩዎችንም ታዳሚው ፊት ወጥተው ትውውቅ ማድረግ ችለዋል፡፡

እሁድ የካቲት 28 ቀን 2013 ዓ.ም ከወልዲያ እና ደሴ ከተሞች በተጨማሪ ሕዝባዊ ስብሰባ የተካሄደበት ሌላኛው ከተማ የአርባ ምንጭ ከተማ ሲሆን፤ በአርባ ምንጭ ከተማ የኢዜማ ምክትል መሪ አንዷለም አራጌ እና የኢዜማ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ምክር ቤት ዕጩ ትእግስት ወርቅነህ በሕዝባዊ ውይይቱ ላይ ተካፋይ ሆነዋል፡፡ ውይይቱ በጋሞ አባቶች ምርቃት የተጀመረ ሲሆን ምክትል መሪው አንዷለም አራጌ፣ ዜግነትን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ ፋይዳው ምን እንደሆነ የመወያያ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ ለመነሻ ከቀረበው የመወያያ ሀሳብ በኋላም ወደ ጥያቄና መልስ የተገባ ሲሆን ከሕዝባዊ ስብሰባው ታዳሚያን ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

በዕለቱ በአርባ ምንጭ ከተማ የሚገኙ የኢዜማ አባላት ለኢዜማ የሰሩትን ሙዚቃ አስተዋውቀዋል፡፡ ኢዜማን በከተማው ወክለው የሚወዳደሩ ዕጩዎችም ተዋውቀዋል፡፡

ኢዜማ በያዝነው ሳምንት መጨረሻ እሁድ መጋቢት 05 ቀን 2013 ዓ.ም በባህር ዳር እና በደብረ ብርሀን ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባ የሚያካሄድ ይሆናል፡፡